★ዴሞክራሲያ★

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

ዴሞ ቅጽ 39 ቁጥር 7 ሰኔ/ሐምሌ 2006 ዓ.ም

## ጽንፈኝነትን ተከላክለን አንድነታችንን እንገንባ

በቅርቡ በተለያዩ ጊዜያት በሀገራችን የተከሰቱት ሁኔታዎች በአገር ሉዓላዊነትና በሕዝባችን አንድነት ላይ አደጋ ያንዣበበ መሆኑን ያመላክታሉ። ከቤኒሻንጉል፣ ከጋምቤላ፣ ከወለጋና ከሌሎች ቦታዎች የአማራ ብሔረሰብ አባላት በዘር ሃረጋቸው ብቻ ከተወለዱበትና ረጅም ዓመታት ከኖሩበት አካባቢ እየተጠረጉ እንዲወጡ መደረጋቸው፤ በባህር ዳር ከተማ በእግር ኳስ ውድድር ወቅት በደጋፊዎች መካከል የነበረውን አለመግባባት ተከትሎ በአማራና በኦሮሞ ዜጎች መካከል በየቦታው ግጭቶች መከሰታቸው፣ በቅርቡ የተወሰኑ አካባቢዎችን ወያኔ ከአዲስ አበባ ጋር ለማጠቃለል ያወጣውን እቅድ በመቃወም የተደረጉት እንቅስቃሴዎች ሁሉ በብሔር/ብሔረ ሰብ ፓለቲካ ላይ የተመሰረቱ መሆናቸው፤ ያለፈ ታሪክን በማስታወስም ሆነ የፈጠራ ታሪክን በማዘጋጀት ከሁሉም አቅጣጫ በተለያዩ ብሔር/ብሔረሰቦች ላይ የቂምና የጥላቻ ዘመቻ በሰፊው እየተካሄዱ መሆናቸው፣ እና ሌሎችም ሆን ተብሎ ሆነ በዘፈቀደ በገዥው መደብና በጽንፈኞች የሚደረጉ ድርጊቶች ወደፊት በአገራችን ሉዓላዊነትና በሕዝባችን አንድነት ላይ ሊመጣ የሚችለውን ከባድ አደጋ የሚጠቁሙ ናቸው። ይህን ጉዳይ ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ አንስተን የተቸንበት ቢሆንም ጉዳዩ አሁንም በጥሞና እንዲታይና ወደመፍትሔው ለመሄድ መነሻ ሊሆን ይችላል በሚል ይህ የዴሞክራሲያ እትም በዚህ ላይ እንዲያተኩር አድርገናል።

በቅድሚያ በተደጋጋሚ እንደተገለጸው ኢትዮጵያ ብዙ ብሔር/ብሐረ ሰቦችን ያካተተች አገር መሆኗ የሚያከራክር አይደለም። የተፈጠረችውም አንዳንዶቹ እንደሚሉት የዛሬ መቶ አመት በአጼ ሚኒልክና በተከታዮቻቸው ሳይሆን ለዓመታት በተካሄዱ የሕዝቦች በይነ ግብር ማለትም በንግድ፤ በጦርነት፤ በግዛት ማስፋፋት፤ በሃይማኖት ማስፋፋት ወዘተ.. በተካሄዱ የእርስ በርስ ግንኙነትና ውህደት ነው። ይህም የጋራ አገር፣ አንድ ሕዝብ የሚለውን ስሜት በሁሉም ላይ ፈጥሮ ለረዥም ጊዜ ቆይቷል።

የተለያዩ ብሔርና ብሔረሰቦች ባህላቸውና ቋንቋቸው ሳይከበር መቆየቱ እንዲሁም እንደሌሎቹ ሁሉ በገዥዎች መብታቸው ታፍኖ የኖረ መሆኑም አሌ ሊባል የሚችል ሐቅ አይደለም። ይህም የተለያዩ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎችን አስከትሏል። በሀገራችን ምስቅልቅል ሁኔታዎችን ፈጥሯል፤ ለአንዳንዶቹም መገንጠል ምቹ ሁኔታን ፈጥሮላቸዋል።

በዓለም ላይ በብሔራዊ መንግስት ተዋቅረው በተለያዩ ስሞች የሚጠሩት አገሮች የተፈጠሩት በረጅም ዓመታት በጦርነት፤ በንግድ፤ በስደት ወዘተ… አማካይነት በሕዝብ መካከል በጠብም በፍቅርም በተደረገ የቅልቅል ብሎም የመስታጋብር ሂደት ውስጥ ሲሆን በተለይም የተለያዩ ቋንቋዎች የሚናገሩ ብሔርና/ብሔረሰቦች ባሉባቸው አገሮች የጋራ አገር የሚለውን ስሜት በሁሉም ዜጎች ውስጥ ቀርጸው በኅብረትና በአንድነት ሊኖሩ የቻሉት የሁሉንም ዜጎች መብትና ጥቅም ለማስከበር በመቻላቸው ነው። የብሔርና ብሔረሰብ መብት ካልተከበረ የሕዝቦች አንድነትና ትብብር ሊፈጠር አይችልም፤ የአገር ሉዓላዊነትና አንድነትንም ሊያናጋ ይችላል። የአገር አንድነት በኃይል አይጠበቅም። የተወሰኑ ዜጎች የአገር አንድነት ይጠበቅ የሚል መፈክር በማሰማታቸው ወይም ጥረት በማድረጋቸው ብቻም የሚረጋገጥ አይደለም ። የአገር አንድነት የብሔርና/ ብሔረሰቦችን ብሶትና ችግር በመካድ የሚገኝ አይሆንም። አምባገነን ኃይሎች ሥልጣን ላይ ለመቀመጥ በሚያደርጉት ሴራና ማጭበርብርም የሚጠበቅ አይሆንም። የአገር አንድነት ሊጠበቅ የሚችለው ብሔር ብሔረሰቦች መብታቸው ተጠብቆ ፤ በቋንቋ፤ በባህል፤ በሃይማኖት ወዘተ… መካከል እኩልነት ሰፍኖ፤ የሁሉም ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብት ተከብሮና ተጠብቆ የጋራ አገር ለጋራ ጥቅም የሚለው ስሜትና በሁሉም ብሔርና/ ብሔረሰብ አባላት ላይ፣ በሁሉም ቋንቋ ተናጋሪዎች እንዲጸርስ ሲደረግ ነው። ይህ እውን ሊሆን የሚችለው ደግሞ የግለሰብ መብትንና የብሔረና ብሔረሰብ የወል መብትን ሚዛኑን በጠበቀ መልኩ ተግባራዊ ማድረግ ሲቻል ነው።

የተለያዩ ቋንቋዎችን የሚናገሩ ወይም የተለያዩ ባህሎችና ልምዶች ያሏቸው ሕዝቦች በአንድ ላይ በሚኖሩበት አገር ውስጥ የብሔርና የብሔረሰብ ችግር በአግባቡ ካልተያዘና መፍትሔ ካላገኘ ልዮነቶቹ ወደ ግጭት፤ ወደ የማያባራ ጦርነትና ደም መፋሰስ፤ እንዲሁም ወደ መከፋፈል የሚሄድበት ሁኔታ ሰፊ መሆኑ ከሀገራችንም ታሪክ ሆነ ሌሎች ብዙ አገሮች ካለፉበት ታሪክ ለመረዳት ችለናል። አሁንም እያየን ነው ወደፊትም ሊቀጥል እንደሚችል የሚያጠራጥር አይደልም። በንጉሡ ሆነ በደርግ ጊዜ ችግሩን የተረዱት ተራማጆች ብሔርና ብሔረሰቦች መብታቸው ይጠበቅ፤ የራሳቸውን እድል በራሳቸው ይወስኑ፤ ችግሮቹ በሠላማዊና በዴሞክራሲያዊ መንገድ ይፈቱ የሚሉ ጥያቄዎችን ያቀረቡትና ትግል ያካሄዱት ችግሩ የአገር ሉዓላዊነትንና የዜጎች አንድነትን በመሠረቱ የሚነካ በመሆኑ ነበር። አንዳንዶች ችግሩን ያመጡት ችግሩ ይፈታ ያሉት ተራማጆች ናቸው የሚል መሠረተ ቢስ ክስ ቢሰነዝሩም ነገሩን ዛሬ ላይ ቆመን ስናየው በዚያን ወቅት ተራማጆቹ የጠየቁት ጥያቄ መልስ አግኝቶ ቢሆን ኑሮ አሁን የሚታየው ችግር በብዙ መልኩ ይቃለል ነበር።

ለብሔር/ ለብሔረሰብ ችግሮች መፍትሔው ዴሞክራሲያ ሥርዓትን እውን ማድረግና የብሔር/ብሔረሰብ ጥያቄን መመለስ ነው። ችግሩ በሰላም ሊፈታ የሚችለው ሁሉም ጉዳዮች አለምንም ገደብ ውይይት እየተካሄደባቸው የጋራ ስምምነትና መግባባት ሲደረስባቸው ነው። ይህ ተግባራዊ ሊሆን የሚችለውም የግለሰብ መብት ሙሉ በሙሉ በተረጋገጠበት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ ነው። ዴሞክራሲያዊው ሥርዓት በግለሰብ ደረጃ ዴሞክራሲያዊ መብትንና ሰብዓዊ መብትን ከማረጋገጥ በተጨማሪ በወል ደረጃ የብሔርና/ ብሔረሰብ መብትን (በቋንቋ

የመናገርና የማዳበር፤ የባህል መብት.. አካባቢን የማስተዳደር መብት ወዘተ..) በማስጠበቅ አንጻር የሚቀርቡትን ጥያቄዎች ማስተናገድ ይጠበቅበታል።

ወያኔ ሥልጣን ሲይዝ እንደቅርጫ በቋንቋ የከፋፈለው ክልል ለብሔር/ብሔረሰብ ጥያቄ መፍትሔ የሚሰጥ ሳይሆን በአገርና በሕዝብ ደረጃ ውስብስብ ችግሮችን የሚቀፈቅፍ ነበር። በርግጥም የተከሰተው ይኸው ነው። አገሪቷን በቋንቋ ክልሎች መከፋፈልና የይስሙላ የፌደራል አስተዳደሮች መመስረት ሕዝብን ከፋፍሎ ለመግዛትና አለጠንካራ ተቃዋሚ ሥልጣን ላይ በአምባገነንት ለመቆየት ይረዳ እንደሁ እንጅ የብሔር/ብሔረሰቦችን መብትም ሆነ ጥቅም አያስጠብቅም። የአገሪቷ ሉዓላዊነትን ሆነ የሕዝቧን አንድነት እንዲጠበቅ አያደርግም። እንዲያውም ከጊዜ ወደጊዜ እየተጠራቀመና እየታመቀ የቆየው ችግር በአንድ ወቅት ፈንድቶ ሕዝብን ወደማያቋርጥና ወደማያባራ የጦርነት ነበልባል ውስጥ ሊያስገባ ይችላል የሚለው ስጋት ጎላ ብሎ ይታያል።

ይህ በወያኔና በተባባሪዎቹ ተንኮል ታቅዶ የተዋቀረውና ሕዝብ በነጻነት አስተያየትና ውሳኔ ያልሰጠበት የቋንቋ ክልልና የይስሙላ የፌዴራል አስተዳደር መዋቅር አደገኛና ሊሰራ የማይችል መሆኑን ለማስረዳት አዋቂ መሆንን አይጠይቅም፡፡ ለመነሻ ወያኔ በቋንቋ ደረጃ ክልሎችን ከፋፍያለሁ ይበል እንጅ እያንዳንዱ ክልል አንድ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑትን ብቻ የሚያጠቃልል አይደለም። የደቡብ ክልል ለምሳሌ ከ10 በላይ የሚሆኑ የተለያዩ ቋንቋዎችን የሚናገሩ ዜጎች ያሉበት ሲሆን በቤኒሻንጉልና ጉምዝ እንዲሁም በጋምቤላ ክልሎች ውስጥ የሚኖሩ ዜጎች አንድ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ አይደለም። ለአማርኛ ተናጋሪዎች አማራ፤ ለኦሮሚያ ተናጋሪዎች የኦሮሚያ ክልል ለትግርኛ ተናጋሪዎች የትግራይ ክልል ተብሎ ይሰየም እንጅ በእነዚህ ሁሉ ክልሎች በቁጥር አነስተኛ የሆኑ የተለያዩ ቋንቋዎችን የሚናገሩ የሌሎች ብሔርና/ ብሔረሰቦች አባላት አሉ። ይህ በራሱ ችግር ነው።

የሌሎች አገሮች ተመክሮዎችን ብንወስድም በቋንቋ ላይ የተመሰረተ የፌዴራል አስተዳደር ለአገር ሉዓላዊነትና ለሕዝቦች አንድነት አደገኛ እንደሆነ እንረዳለን። ቋንቋን መሠረት ያደረገ የፌዴራል አስተዳደርን ያስተናገዱ ጥቂት አገሮች አደገኛ ሁኔታ አጋጥሟቸዋል። ለረጅም ዓመታት በአምባገነን አገዛዝ ስር የቆዩ እንደ የቀድሞ ዮጎዝላቪያ፤ ቼኮዝላቪያና እንዲሁም በሶቪየት ሕብረት ስር የነበሩ ሪፐፕሊኮች አምባገነን የነበረው ማእከላዊ መንግሥት ሲፈርስ ወይም በሌላ ሲተካ ተገነጣጥለዋል። በተገነጠሉ ማግስት በራሳቸው ውስጥ ያሉ ውህዳን ብሔረሰቦች በማመጻቸው ያልተቋረጠ ደም መፋሰስ ያጋጠማቸው መሆኑም ታይቷል። በአፍሪካም ውስጥ በተለያዩ አገሮች በቅርቡ በደቡብ ሱዳን የደረሰውን ጨምሮ ይኸው ችግር ጎላ ብሎ ታይቷል።

በአንድ አገር ውስጥ የሚኖሩ ዜጎች የተለያዩ ቋንቋዎች በመናገራቸው ብቻ በፌዴራልም ሆነ በሌላ ደረጃ የሚሰየሙ የአስተዳደር ክልሎች በቋንቋ መከፋፈል አለባቸው የሚል ሀሳብ አሳማኝ ሊሆን አይችልም። በዓለም ላይ የሚነገሩ ቋንቋዎች ከ6000 በላይ ሲሆን ዓለም በ6000 አገሮች ትከፈል ወይም 6000 የሚሆኑ የፌዴራል አስተዳደር ክልሎች ይመሥረቱ የሚል መከራከሪያ ማንንም ሊያሳምን የሚችል አይደለም። በአገራችንም ከ 84 ቋንቋዎች

በላይ ስለሚነገር 82 *የቋንቋ ክልሎችና የፌደራል አስተዳደሮች ይኑሩ የሚል ሀሳብ ተግባራዊ ሊሆን እንደማይችል ግልጽ ነው።*

አንድ ቋንቋ የሚናገሩ ዜጎች ሁል ጊዜ በአንድ አገር ተጠቃለው አይኖሩም፤ እንግሊዘኛ የሚናገሩ ዜጎች በእንግሊዝ፤ በካናዳ፤ በአሜሪካ በአውስትራሊያና በኒውዚላንድ እንዲሁም በሌሎች ቦታዎች ይኖራሉ። አረቦች በ20 አገሮች ውስጥ ይኖራሉ። ከእነዚህ ውስጥ አንዳንዶቹ ኩታ ገጠም በሆነ አካባቢዎች ነው። በብዙ አገሮች የፌዴራል አስተዳደር ክልሎች ቋንቋን መሠረት ያደረጉ አይደለም። ለምሳሌ ስዊዘርላንድ አራት የተለያዩ ቋንቋዎች - ጀርመን፣ ፈረንሳይ፣ ጣሊያንና ሮማንስ የሚነገርባት አገር ስትሆን ካንቶን ተብለው በሚጠሩ 26 የ ፌዴራል የክልል ግዛቶች ውስጥ ተበትነው ይገኛሉ። በስዊዘርላንድ የተለያዩ ቋንቋ ተናጋሪዎች በራሳቸው ቋንቋ የመናገር ባህላቸውን የማዳበር ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር መብት ቢኖራቸውም በአንድ የአስተዳደር ክልል ውስጥ የተወሰኑ አይደሉም። በርካታ ብሔረሰቦችን አስተናግዳ የያዘችው ህንድም ያኗት ፌዴራል ክልሎች የተከለሉት ቋንቋን ወይም ብሔርና/ብሔረሰብን መሰረት አድርገው አይደለም። በህንድ ለምሳሌ ከ 780 የተለያዩ ቋንቋዎች የሚናገሩ ብሔርና ብሔረሰቦች ያሉ ሲሆን አገሪቷ በ29 የፌዴራል አስተዳደሮችና 7 በሚሆኑ የአንድነት ግዛቶች ተከፋፍላለች። አከፋፈሉ ቋንቋን መሠረት ያደረገ ሳይሆን አካባቢና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን መሠረት በማድረግ የተዋቀረ ነው። ስለሆነም በብዙ አገሮች የፌዴራል አስተዳደር አካቢዎች የተከለሉት ቋንቋን ወይም ብሔር/ብሔረሰብን መሠረት በማድረግ አይደለም ።

በቋንቋ ላይ የተመሠረተ የክልል አስተዳደር በማዕከል ሥልጣን የያዘው አምባገነን ኃይል እስከ ሆነ ድረስ የብሔርና ብሔረሰብ መብትን በተሟላ መልኩ የማያስጠብቅ ከመሆኑም በላይ ከሕዝቦች አንድነትና ከአገር ሉዓላዊነት አንጻር ጉዳቶች እንዳሉት መረዳት ያስፈልጋል። በመጀመሪያ ደረጃ በአንድ ክልል ነዋሪ የሆኑ ሌላ ቋንቋ ተናጋሪዎችን እንደ ባዕድ ማየት ይመጣል፤ ጠራርጎ ለማስወጣትም እንቅስቃሴ ይደረጋል። ሁለተኛ በቅድሚያ ለክልሌ፤ ለብሔረሰቤ የሚለው ሥነ ልቦና ስር ሲሰድ ለሌሎች ክልሎች የማሰብና ወገንተኛ የመሆን ስሜትን ያጫጫል። ለዚህ ምሳሌ ሊሆን የሚችለው በቅርቡ በአዲስ አበባ ዙሪያ የተወሰኑ ክልሎችን ወደ አዲስ አበባ ክልል ለመጠቅለል ወያኔ የወሰደውን እቅድ በመቃወም በኩል የተፈጠረው ክስተት ነው። በመጀመሪያ ደረጃ ወያኔ ከሕዝብ ይሁንታና ከሕግ ውጭ አርሶ አደሮችን የሚያፈናቅለውንና የሚያደኸየውን እንዲሁም ለወያኔ ባለሥልጣናት ኪስ ማደለቢያ ሊሆን የታቀደውን ፖሊሲ መቃወም የማንኛውም ኢትዮጵያው ግዴታ ነው። ከፍተኛ ተቃውሞ አካሄዶ ድርጊቱን ማስቆም የሁሉም ኢትዮጵያዊ ኃላፊነት ነው። ዓላማው ግን ለምን አርሶ አደሮች ይፈናቃሉ ለምን አለ ሕግና አለ ስምምነት መሬታቸው ይቀማል ከሚል መሆን አለበት እንጅ መሬት ከኦሮሚያ ክልል ወደ አዲስ አበባ በመጠቃለሉ መሆን የለበትም አዲስ አበባም ሆነ የኦሮሚያ ክልል የኢትዮጵያ ንብረቶች ናቸውና። በኦሮሚያ ክልል የተነሳው ተቃውሞ ለምን መሬት ከኦሮሚያ ክልል ይወሰዳል የሚል ብቻ በመሆኑ ተቃውሞው በሌሎች ብሔረና ብሔረሰቦች አልታጀበም። መሠረቱ ብሔራዊ ስሜትነት ቀስቅሶ ጉዳዩን ሁሉም በባለቤትነት ወስዶት ተቃውሞ ማድረግ ሲገባ ይህ ሳይሆን ቀርቷል። ይህ ክፍተት የክልል ስሜት

የፈጠረው ነው። ሦስተኛ የቋንቋ ክልል በብሔረና ብሔረሰብ መካከል የማያቋርጥ ጥላቻንና ልዩነትን ያስፋፋል፤ ዜጎች ለመብታቸው በአንድ ላይ እንዳይታገሉ ጋሬጣ ይፈጥራል። የመገንጠል ስሜትን ያጠናክራል፤ ለመገንጠልም ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል።

ወያኔ በፈጠረልን የክልል ሥነ ልቡናዊ ጉዞ መጓዙን ከቀጠልን የብሔር/ብሔረሰብ መብት ሊጠበቅም ሆነ ሁላችንም የምንፈልገውና የምንታገልለት ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብታችን ሊከበርልንና እውን ሊሆን አይችልም። ወያኔ የከፍፍል ፖሊሲውን እያጠናከረ በአምባገነንነት መግዛቱን ይቀጥላል። እኛም እንደታፈንን እንኖራለን። ተደጋግሞ እንደተነገረው ወያኔ የቋንቋ ክልሎችን አዋቅሮ ተግባራዊ ያደረገው ሕዝብን በመከፋፈልና በማዳከም በሥልጣን ላይ ሊቆይ የሚችልበትን ጊዜ አስተማማኝ ለማድረግ ነው። ይህንን የሚያደርገው በአስተዳደራዊ ወይም ፖለቲካዊ ሴራ ብቻ አይደለም። ጽንፈኛ አመለካከት ያላቸውን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በመደገፍና በማንቀሳቀስ ጭምር ነው። ጽንፈኛ አመለካከት ያላቸው ክፍሎች ያለፈ ክስተትን በማስታወስ በብሔር/ብሔረሰብ መካከል የበቀል እርምጃ እንዲወሰድ ይቀሰቅሳሉ፤ ጥላቻን በማስፋፋት ሕዝብ ወደ አንድነት እንዳይመጣ ይጥራሉ። "በአንድ ጽንፍ ሚኒልክ ኦሮሞን ጨፍጭፏል፤ ስለሆነም አማራን ማጥፋት አለብን የሚለውና በሌላ ጽንፍ የኦሮሞን ሕዝብ ወደ መጣበት ወደ ማዳስካር ጠርገን እናስወጣለን.... ወዘተ..." የሚሉት የጥላቻና የክፍፍል ቅስቀሳዎች በጠባብና ጽንፈኛ ብሔረተኞች የሚተስተጋቡ ሲሆኑ ቤንዚን ተርከፍክፎባቸው እንዲቀጣጠሉ የሚደረጉት በወያኔ ነው። ይህን መገንዘብና ጽንፈኞችን ሁሉ መታገል የአገር አድን ትግሉ ዋና አካል ነው።

ቋንቋን መሠረት ያደረገው የክልል ፌዴሬሽን የብሔር/ብሔረሰብ መብትን በተሟላ መልኩ ማስጠበቅና አለማስጠበቁ አከራካሪ ቢሆንም የሁሉም ብሔር/ ብሔረሰቦች ዜጎች በግለሰብ ደረጃ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብታቸው በአምባገነኑ ጨካኝ ቡድን የታፈነ መሆኑ ግን አሌ የሚባል አይደለም። ሁሉም በወያኔ አምባገነን አገዛዝ እየማቀቁና እየተረገጡ ይገኛሉ። ነጻነታቸውን ያጡት፤ መብታቸውን የተገፈፉት ሁሉም ናቸው። ሁሉም በአንድ ላይ እስካልተነሱ ድረስ ደግሞ በአምባገነን ሥር መማቀቁ ይቀጥላል።

መገንጠልን እንደ ብቸኛ አማራጭ በመውሰድ ትግል እናካሂዳለን የሚሉ ጽንፈኛ ብሔረተኞች የሚያካሂዱት እንቅስቃሴ በአገርና በወገን ላይ የሚቀፈቅፈው ችግር ከባድ መሆኑን መረዳት አለባቸው። መገንጠል ለብሔር/ብሔረሰብ ጥያቄ በራሱ መፍትሔ ሊሆን እንደማይችልና ለሕዝቡም ሰላምና ዴሞክራሲ እንደማያስገኝ ሩቅ ሳንሄድ ከኤርትራ ሁኔታ መረዳት የሚቻል ይመስለናል። ለመገንጠል የሚንቀሳቀሰው ክልል በውስጡ የተለያዩ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ ዜጎችን እስከያዘ ድረስና በረዥም ጊዜ የእርስ በርስ ግንኙነት እርስ በርሱ የተዛመደውና የተጋመደው ሕዝብ በአካባቢው ነዋሪ እስከሆነ ድረስ መገንጠል ያልተቋረጠ ግጭትንና ጦርነትን ሊያስከትል እንደሚችል ከወዲሁ መገመት ያስፈልጋል።

መፍትሔው ምንድ ነው? የሚለው ተገቢ ጥያቄ ነው ። ይህን ከመመለስ በፊት የወደፊቱን ሁኔታ በመላ ምትም ቢሆን መዳሰሱ ለሚኖረን ግንዛቤና መውሰድ ለሚኖርብን ርምጃ ጠቀሜታ ይኖረዋል። ምን ሊከሰት ይችላል? የሚለው በትክክል መናገር ቢያስቸግርም ከሁለት ሁኔታዎች አንደኛው ሊፈጠር እንደሚችል መገመት ይቻላል። ወያኔ ውስጣዊ አንድነቱን ጠብቆ፤ የወታደራውንና የፓሊቲካ የበላይነቱን ይዞ፤ የከፍፍል ሴራውን ተግባራዊ አድርጎ መቀጠል ከቻለ ለረዥም ጊዜ የኢትዮጵያን ሕዝብ ሙብት ረግጦ ሥልጣኑን ጨብጦ ይቀጥላል። በተበታተነ የሕዝብ ግፊት ወይም በውስጣዊ ችግር ምክንያት ሥልጣኑ ከተንኮታኮተ የኢትዮጵያ ህልውናና አንድነት ከአደጋ ነጻ ሊሆን ይችላል ብሎ መገመትም ይከብዳል።

መፍትሔው የሚገኘው በሁሉም ወገን የሚገኙትን ጽንፈኛ አመለካከቶች አስወግዶ በአቢይ ጉዳዮች ላይ ተስማምቶ በጋራ መንቀሳቀስ ሲቻል ነው። ለሁሉም ብሔረሰቦች እንዲሁም ለአገሪቷ ሠላም ዴሞክራሲና ፍትሕ የሚገኝበትን ሁኔታ መሻት፤ ሁሉም ሀገሬ ወገኔ የሚለውን አመለካከት በልበናው አስርጾ እጅ ለእጅ ተያይዞ የሚነሳበትን መንገድ መፍጠር ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ ብሔርና ብሔረሰብ የለም ፤ የሚጠየቀው የሙብት ማስከበር ጥያቄ አግባብነት የለውም ወይም ሙብትን መጠየቅ ጸረ ኢትዮጵያዊነት ነው፤ ጸረ አንድነት ነው ብሎ በብሔርና/ብሔረሰቦች ላይ መዝመት ፣ የወቅቱን የኢትዮጵያን ሁኔታ ያላገናዘበ ከመሆኑ ባሻገር ለኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነትና ለአገሪቷ ሉዓላዊነት አደጋን የሚጋብዝ ነው። ይህንን ጽንፈኛ አመለካከት የሚገፉ ወገኖች በብርቱ እንዲያስቡበትና አመለካከታቸውን እንዲቀይሩ አበክሮ መታገልና መስራት ያስፈልጋል። በራስ ቋንቋ ለመናገር የራስ ባህል እንዲከበር መጠየቅ፤ ራስን በራስ ለማስተዳደር መንቀሳቀስ የሚነቀፉ ወይም የሚፈሩ መሆን የለባቸውም። እነዚህ ጥያቄዎች በትክክል በሥራ ላይ ከዋሉ፤ በብሔርና ብሔረሰቦች መካከል ያለው የእኩልነት ስሜት የሚረጋገጥበት ብሔርና ብሔረሰቦችን ይበልጥ የሚያዛምድበትና የሚያያዝበት ሁኔታ ይፈጥራል፤ ሀገራዊ ስሜት በሁሉም ላይ እንዲሰርጽ ያደርጋል።

የብሔራዊ ቋንቋ ጥያቄም ልዩነት የሚፈጥር መሆን የለበትም። በሕዝብ ስምምነት መሠረት መሆን አለበት እንጂ፤ በአንድ አገር ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ብሔራዊ ቋንቋዎች ሊኖሩ ይችላሉ። ዋናው ነገር የብዙኀኑ መገናኛ ለመሆን ብቃት ማግኘቱና ብዙኀኑ የሚፈቅዱት መሆኑ ላይ ነው። አማርኛ ብሔራዊ ቋንቋ በመሆኑ አማራው ሌላውን ሊጨቁን ይችላል ወይም በሌላው ላይ የበላይነት አለው የሚለው አመለካከት ጊዜ ያለፈበትና ተጨባጭ ሁኔታውን የማያገናዝብ ነው። ብሔራዊ ቋንቋ ሕዝብን እርስ በርስ የሚያገናኝ የመግባቢያ ቋንቋ ነው። እንግሊዘኛ በታሪክ አጋጣሚ በተለያዩ ወቅቶች በተለያዩ አገሮች በመስፋፋቱ ዛሬ አብዛኛውን የዓለም ክፍል የሚያገናኝ ዓለም አቀፍ ቋንቋ ሆኗል። አማርኛም ብሔራዊ ቋንቋ ሊሆን የቻለው በታሪክ አጋጣሚ ነው። በአሁኑ ወቅት አማርኛ ብሔራዊ ቋንቋ የሆነው በአማሮች ብቻ ሳይሆን በብዙዎች ብሔር/ብሔር ሰብ አባላት ተደግፎ ነው። ከብሔራዊ ቋንቋነት አልፎም በአካባቢው ሕዝብ ፍላጎት ስምምነትና ውሳኔም ለተወሰኑ ክልሎች ዋና የክልል ቋንቋ ሆኖ በማገልገል ላይ ይገኛል። ነገ ኦሮምኛ ወይም ሌላ ቋንቋ ተጨማሪ ብሔራዊ ቋንቋ እንዲሆን ሀሳብ ቀርቦ የብዙኀኑ የኢትዮጵያን

ሕዝብ ፍላጎትና ውሳኔ የሚያገኝ ከሆን ይህ ጉዳይ ክርክር ሊያስነሳም ሆነ የልዩነት ነጥብ ሊሆን አይገባም። ሁለትም ሦስትም ብሔራዊ ቋንቋዎች በአንድ አገር ውስጥ መነገር ይችላሉ።

በሌላው ጽንፍ መገንጠልን እንደመፍትሔ የሚያቀነቅኑ እንዲሁም ክልልን ወይም ብሔር/ብሔረሰብን ከአገርና ከወገን የሚያስቀድሙ፤ ብሔር/ብሔረሰብን ከአገር ነጥለው የሚያዩ ጽንፈኞች የያዙት አመለካከት አደገኛ መሆኑን ተረድተው አመለካከታቸውን እንዲያስተካክሉ መገፋፋትና መታገል ያስፈልጋል። የሚያቀነቅኑት ሀሳብ ተግባራዊ ቢሆን እንኳ ከፍተኛ ቀውስንና የረዥም ዓመታት ደም መፋሰስን ሊያስከትል እንደሚችል ሳይሰልቹ ማስገንዘብ ያስፈልጋል። የአንድ ብሔር/ብሔረሰብ አባልነትን ከኢትዮጵያዊነት ነጥሎ የማየትን አመለካከት ለማረምና ለማስተካከል ትግል ማካሄድ ያስፈልጋል። የአገር ዜግነት ማለትም ኢትዮጵያዊነትና የብሔረ/ብሔረሰብ አባልነት የሚነጣጠሉ አይደሉም፤ አንደኛውን አስቀድመን ሌላኛውን የምናስከትልበትም ሁኔታም የለም፤ ሁለቱም የአካሎቻችን ክፍሎች ናቸው፤ ልንነጥላቸው አንችልም።

በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ከፍተኛ በደል ወንጀል እየፈጸመ ያለውን አስከፊውን የወያኔን አገዛዝ ለአንዴም ለሁሌም አሽንቀጥሮ ለመጣልና ሁላችንም መብታችን የሚከበርበት፤ እኩልነታችን የሚረጋገጥበት ፍላጎታችን የሚሟላበትና አገራችንና ሕዝባችን በእድገትና በብልጽግና ጎዳና የሚራመዱበትን ሥርዓት ለመፍጠር ጽንፈኝነትን አስወግደን እጅ ለእጅ ተያይዘን ትግላችንን እንቀጥል የሚለው ወቅታዊ የኢሕአፓ መልእክትና ጥሪ ነው። ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ሁላችንም የድርሻችንን እናድርግ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በትግሉ መብቱን ይቀዳጃል፤ አንደነቱን ያስከብራል!!!